# “የአፍሪካ አንበሳ” - ኢትዮጵያ - ሚሊየነሮችን በማፍራት ጎዳና

እንደሻው ከበረ

Tigrai Online Feb. 28, 2014

ባለፈው ሰሞን **Recorder Report** የተሰኘ ተቋም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከአፍሪካ አገራት በፈጣን እድገቱ በቀዳሚነት እንደሚጠቀስ በመግለፅ ባወጣው ዘገባ ላይ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከሰሃራ በታች ካሉ ግዙፍ ኢኮኖሚ ካላቸው የአፍሪካ አገራት በአምስተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መግለፁ ይህን ፅሁፍ እንዳዘጋጅ እንዳነሳሳኝ በቅድሚያ ለአንባቢዎቼ  ለመግለፅ እወዳለሁ።

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ መንግስት በተግባር ላይ ያዋላቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ውጤታማነት ዋነኛ ማሳያ የሆነው ይህው የአገሪቱ ፈጣንና ተከታታይ ኢኮኖሚያዊ እድገት በአሁኑ ወቅት የአገሪቱን ገፅታ በመገንባት ረገድ ከፍተኛውን አስተዋፅኦ እያበረከተ መሆኑ መቼም ከማናችንም እይታ የተሰወረ አይደለም።

ይህን ልል የቻልኩበት ዋናው ምክንያት የተለያዩ አለም ዓቀፍ መገናኛ ብዙሃንም ሆነ አለም ዓቀፍ ተቋማት በየትኛውም አጋጣሚ ኢትዮጵያን የተመለከተ ማናኛውንም አይነት መረጃ ባወጡበት አጋጣሚ ሁሉ ይህንኑ ያለ ነዳጅም ሆነ ያለ አንዳች የተፈጥሮ ሃብት የተመዘገበ የአገሪቱን ፈጣንና ተከታታይ ኢኮኖሚያዊ እድገት ያላደነቁበት አጋጣሚ የለምና።

በርካቶች እንዴያውም ኢትዮጵያን በአሁኑ ወቅት እየገነባችው ካለው ግዙፍና ጠንካራ ኢኮኖሚ ጋር አያይዘው **“The Africa’s Lion” (የአፍሪካ አንበሳ)** በሚል ከሰየሚቸው አገራት በቀዳሚነት ይጠቅሷታል።

የኢትዮጵያ መንግስት በአሁኑ ወቅት አገራችን በአፍሪካ ግዙፍና ጠንካራ ለመሆን የበቃ ኢኮኖሚ እንድትገነባ ማድረግ የቻለው በዋነኝነት ከአገሪቱና ህዝቦቿ ይገኙበት ከነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ተነስቶ በቀየሰው ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መስመር መሆኑ ይታወቃል፡፡

መንግስት ያለምንም የተፈጥሮና የነዳጅ ሃብት በሌለበት ሁኔታ  ላለፉት አስር ተከታታይ ፈጣንና ተከታታይ ኢኮኖሚያዊ እድገት በማስመዝገብ በአፍሪካ በጠንካራና በግዙፉነቱ ኢኮኖሚ ለመጠቀስ የበቃ ኢኮኖሚ መገንባት ከጅምሩ ግብርናና ገጠርን ማእከል ያደረገ የልማት ስትራጂ በመቅረፅ ነበር፡፡

ይህ የልማት ስትራቴጂ ውጤታማ ለመሆን የበቃው አገሪቱ ያላትን ሰፊ የመሬት ሃብትና የሰው ጉልበት በላቀ ደረጃ ለመጠቀም ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩ በተጨማሪ በሂደት ንግድና ኢንዱስትሪው ፈጣን በሆነና ቀጣይነት ባለው መንገድ እድገት እንዲያስመዘግብ እንደሚያደርግ ታሳቢ በማድረግ ነበር፡፡

ኢትዮጵያ ሰፊ የሰው ሃይል ያላት አገር እንደመሆኗ መጠን ከዚህም ህዝብ መካከል በርከት ያለው ቁጥር ያለው ማለትም ወደ 85 በመቶው ያህል የህብረተሰብ ክፍል በገጠር እንደሚገኝ  ይታወቃል ፤ ይህም ባለፉት አመታት በአገሪቱ ተግባራዊ የተደረገው የግብርና መር የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጂ በርካታውን ህዝብ በልማቱ እንዲሳተፍና ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ውጤታማ እንዲሆን እንዳስቻለው ይጠቀሳል፡፡

መንግስት የኢኮኖሚ ፖሊሲውንና ስትራቴጂውን ገና ከጅምሩ ተግባራዊ ሲያደርግ ዋነኛው አላማው የነበረው አገሪቱ ለረዥም አመታት ከቆየችበት የተመፅዋችነት ፣ የሁዋላ ቀርነትና የድህነት ማጥ ውስጥ እንድትወጣ ለማድረግ የሚያስችል ፈጣን ልማት በማስመዝገብ ህዝቡን ከልማቱ በየደረጃው ተጠቃሚ ማድረግና በሂደትም የዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ስርአት መፍጠር ነበር፡፡

ውጤታማ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በመቅረፅ ለተግባራዊነቱ ህዝቡን በቁርጠኝነት በማንቀሳቀስ ያለ ምንም የተፈጥሮ ሃብት ላለፉት አመታት በአፍሪካ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ፈጣንና ተከታታይ ኢኮኖሚያዊ እድገት ማስመዝገብ የቻለው የኢትዮጵያ መንግስት ታድያ በአሁኑ ወቅት ቀደም ሲል የተጠቀሱትን የህዝቡን ተጠቃሚነት የማረጋገጥና የዳበረ ኢኮኖሚ መገንባት የሚሉ አላማዎቹን በተሟላ ሁኔታ ለማሳካት በቅቷል፡፡

ግብርና  መር የኢኮኖሚ ፖሊሲው አገሪቱ ከውጭው አለም ጋር የነበራትን የንግድ ልውውጥ በማሳደግ ለረዥም ጊዜ በቡና ምርት ብቻ ተይዞ የነበረው የወጭ ንግድ የአበባና የፍራፍሬ ምርቶችን ጨምሮ የተለያዩ የቅባት እህሎችና ሌሎች የግብርና ምርቶች ታክለውበት ከፍ ያለ የውጭ ምንዛሬ ለአገሪቱ በማስገኘት ላይ ይገኛል፡፡

አርሶ አደሩም በገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ማምረት መጀመሩም አገሪቱ ለውጭ ገበያ የምትልከው የምርት መጠን በዓመት 50 በመቶ እንዲጨምር እንዳደረገው በቅርብ የመስኩ ባለሙያዎች ይፋ ያደረጉ ሲሆን የግብርናው ዘርፍ መንግስት በቀየሰው ፖሊሲ በገበያ መር ስትራቴጂ እንዲመራ መደረጉ በአርሶ አደሩ የአኗኗር ዘይቤ ላይ ከፍተኛ የሆነ ለውጥ አምጥቷል።

ባለፉት አመታት በአገሪቱ በግብርናው ዘርፍ ከሰብል ምርት ወደ ገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርት ማምረት የተደረገው ሽግግር ከቅርብ አመታት ወዲህ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት በኩል መካሄድ የጀመረ ዘመናዊ የግብርና ምርት ገበያ ስርዓት ተግባራዊ እንዲሆን ያስቻለ ሲሆን ይህም ዘመናዊ የግብይት ስርአት ለሌሎች የአፍሪካ አገራት የግብርና ዘይቤ ከፍተኛ አርአያነት እንዳለው ሲገለፅ እንሰማለን ።
በኢትዮጵያ አርሶ አደሩ ለገበያ ፍጆታ የሚውሉ ምርት እንዲያመርት መደረጉ የሚያስገኘው ጥቅም የሰብል ምርት ያመርት ከነበረበት ጊዜ ይልቅ ምርታማነቱን ለማሳደግ የስራ ተነሳሽነቱ እንዲጨምርና መሬቱንና የምርት ግብአቱንም በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲያውል በማድረግ አርሶ አደሩን ከመቼውም ጊዜ በላይ በአገራዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ አድርጎታል።

ይሁን እንጂ የአገሪቱ የወጪ ንግድ ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን ከቅርብ አመታት ወዲህ ወርቅን የመሳሰሉ ማእድናትን ኤክስፖርት በማድረግ የአገሪቱን የወጪ ንግድ ገቢ ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

ከዚህ ይበልጥ ግን ኢትዮጵያ ካለፉት ሶስትና አራት አመታት ወዲህ የህዳሴውን ግድብ ጨምሮ እየገነባቻቸው ያሉ ትላልቅ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድቦች ጎወደፊት ጎረቤቶቿን ጨምሮ ለበርካታ የአፍሪካ አገራት የኤሌክትሪክ ሃይል በመሸጥ የኢኮኖሚ ገቢዋን ይበልጥ በሰፊ መሰረት ላይ ለማቆም ያዘችው እቅድ ሲሆን ይህም ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ እድገት ትራንስፎርሜሽን እንደሚፈጥርላት ይታመናል፡፡

እነዚህና ቀደም ሲል የተጠቃቀሱት አብነቶች በኢትዮጵያ ተግባራዊ የሆነውን የልማታዊና የዴሞክራሲያዊ ስርአት ስኬት የሚያሳይ ሲሆን  በአገሪቱ እስካሁን የተመዘገበው ፈጣንና ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገትም መንግስት የትምህርትና የጤና አገልግሎቶችን በስፋት ለዜጎች ያዳረሰበትን ሰፊ የመሰረተ ልማት አውታር ግንባታ በበቂ ሁኔታ እንዲዘረጋ ያደረገ አቅም ፈጥሯል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘም ባለፈው ሰሞን መቀመጫውን እንግሊዝ ያደረገ አንድ New World wealth የተሰኘ ቡድን ባካሄደው ጥናት ይፋ እንዳደረገው ከሆነ ደግሞ ኢትዮጵያ ባለፉት አመታት ያስመዘገበችው ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከአፍሪካ አገራት መካከል በርካታ ሚሊዮነሮችን በፍጥነት በማፍራት  የቀዳሚነት ስፍራ እንድትይዝ አስችሏታል።

ድርጅቱ በዚሁ የጥናቱ ውጤት ላይ ታድያ በኢትዮጵያ እኤ.አ በ2007 የሚሊየነሮች ቁጥር 1 ሺህ 300  እንደነበሩ ጠቅሶ በአገሪቱ ባለፉት ስድስት አመታት እኤአ በመስከረም ወር 2013 ላይ ይህው አህዝ በፈጣን ሁኔታ እድገት በማሳየት የኢትዮጵያውያን ሚሊዮነሮች ቁጥር 2 ሺህ 700 መድረሱን ይፋ አደርጓል።

የኒው ወርልድ ዌልዝ ጥናት በኢትዮጵያ የሚሊየነሮቹ ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት ለመጨመሩ ዋነኛ ምክንያት በሚል የጠቀሰውም በአገሪቱ የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት /GDP/ እድገት መጨመር ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው።

ይህው ድርጅት አያይዞም ኢትዮጵያ ባለፉት አስርት አመታት ወዲህ ያስመዘገበችው የኢኮኖሚ እድገት በአሁኑ ወቅት ሰሀራ በታች ከሚገኙ የአፍሪካ አገራት ለአስር ዓመታት መልካም ዕድገት በማሳየት ኬንያን በመቅደም ግዙፍ ኢኮኖሚ በመገንባት ረገድ በአምስተኛ ደረጃ ላይ እንደደምትገኝ መግለፁ የመንግስትን ፖሊሲና ስትራቴጂ ውጤታማነት በድጋሚ የሚያረጋግጥ ነው ።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ እያስመዘገበች ያለችውን ኢኮኖሚያዊ እድገት ጨምሮ በመሠረተ ልማት፣ በግብርና፣ በጤናውና በትምህርቱ ዘርፍ ያሳየችውን እምርታና ከፍተኛ ለውጥ ከማንም ሊደበቅና መካድ ያልተቻለ ገሃድ እየሆነ መጥቷል፡፡

ኢትዮጵያ ከአፍሪካም አልፎ በዓለማችን በፍጥነት በማደግ ላይ ከሚገኙት አገራት ተርታ የምትገኝና በሚያስደንቅ የለውጥ ጎዳና ላይ ያለች ከመሆኗ አነፃር በአሁኑ ወቅት ገንዘባቸውን በኢትዮጵያ ማፍሰስ የሚፈልጉ የውጭ ባለ ሀብቶች ቁጥር እንዲበራከት አድርጎታል፡፡
ስለሆነም በኢትዮጵያ ላለፉት አስር አመታት በፈጣንና በተከታታይ ሁኔታ የተመዘገበው ኢኮኖሚያዊ እድገት ለመጪዎቹ ተከታታይ አመታትም መመዝገቡን እንደሚቀጥል የአለም ባንክም ሆነ ሌሎች የገንዘብ ተቋማት መግለፃቸውን እንደቀጠሉ ናቸው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞም የኢትዮጵያ መንግስትም በኢትዮጵያ በዘንድሮው አመት በአገሪቱ ከተጠበቀው በላይ የግብርና ምርት መገኘቱ በሚቀጥለው አመት የሚመዘገበውን የኢኮኖሚ እድገት ባለሁለት አሀዝ እንዲሆን እንደሚያደርገው በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለ ማሪያም ደሳለኝ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ላይ ማስታወቃቸው ይታወሳል፤ ይህም በአገሪቱ በርካታ የሥራ እድልን በመፍጠር፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የንፁሕ ውኃ፣ የመፀዳጃ አገልግሎቶችን እንደዚሁም የመንገድ አውታሮችን በመዘርጋት ረገድ የተጀመሩና የመጡ ለውጦችም ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የሚያደርግ ይሆናል ።

መንግስት ላለፉት ሶስት አመታት ተኩል በላይ በተግባር ላይ ያዋለው የአምስት አመቱ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ኢንዱስትሪው በኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነቱን ሚናውን ለመረከብ የሚያስችሉ ዝግጅቶች የሚጠናቀቁበት ከመሆኑ አንፃር ይህም በመልካም አፈፃፀም ላይ ይገኛል፡፡